- ቢሮው እና ኮርፖሬሽኑ ወረቀት አልባ በሆነ ዘመናዊ ሲስተም አገልግሎት እየሰጡ ነው፡



በገጽ---1---ይመልከቱ

የመንግስት ቤቶችን መረጃ በዘመና ዊቴክኖሎጂ የማደራጀት ስራው ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተገለጸ።



በገጽ---2---ይመልከቱ

የ54ቱ ማህበራት የስራ ሂደትተገመገመ።



በገጽ---1---ይመልከቱ

የመንግስት እና የግል አጋርነት (PPP) ፕሮጀክት ትግበራ የ2017 በጀት አመት የ6 ወር አፈፃፀም ተገመገመ።



በገጽ---3---ይመልከቱ

ኤዲተርና ዝግጅት ክትትል

የንጋትኮከብ አባቡ

አዘጋጆች

አማረ ካሳ

ጌታሰው ብርሃን

ምክትል አዘጋጅ

ፍሬህይወት እሸቱ

ፎቶግራፈር

ሀዊ ከሊል

ጎንቹ በቀለ

ለይአውትና ግራፊክ ዲዛይን

አዲስአለም ተከስተ
0925455932

**በውስጥ ገጾች** **ገፅ**


- ቢሮው እና ኮርፖሬሽኑ ወረቀት አልባ ---- -------------1
- የ54ቱ ማህበራት የስራ ሂደት----------------------1
- የመንግስት ቤቶችን መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማደራጀት------2
- የመንግስት እና የግል አጋርነት [PPP] ፕሮጀክት ትግበራ---------3
- በአዲስ አበባ ቤቶች ልማትኮርፖሬሽን------------------3
- ወደ ጋራ መኖሪያ ቤት እየገቡ የሚገኙ የልማት ተነሺዎችን--------4
- በቢሮው የተካሄደው ሪፎርም ያመጣው-----------------5
- የመንግስት ፣ የጋራ እና የግል መኖሪያ እንዲሁም-----------6
- ቢሮው በቤት ልማት ስትራቴጂና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች---------6
- ሙያና ሙያተኞች በስነምግባር ካልታነፁ-----------------7
- ቢሮው በቋሚነት ለሚደግፋቸው---------------------8

## ቢሮው እና ኮርፖሬሽኑ ወረቀት አልባ በሆነ ዘመናዊ ሲስተም አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡

የቤቶች ልማት አስተዳደር ቢሮ እና የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ዘመናዊ የደንበኞች አገልግሎት እና ቅሬታ መቀበያ ሲስተም በማልማት በወረቀት አልባ ዘመናዊ ሲስተም ደንበኞችን በአንድ መስኮት በማስተናገድ በሙሉ አቅም እየሰሩ ነው።



በአንድ መስኮት የሚሰጠው ዘመናዊ አገልግሎት አሰራሩን ግልፅ ተአማኒ ፣ የተቀላጠፈ እና አገልግሎት ፈልገው የሚመጡ ግለሰቦች የሚያነሷቸውን ተገቢነት ያላቸው ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች በአጭር ጊዜ መልስ የሚያገኙበት መሆኑ ተገልጿል።

የተጀመረው ዘመናዊ አገልግሎት ከዚህ ቀደም በወረቅት (Manual) ሲሰራ የሚፈጠረውን አላስፈላጊ ምልልስ በመቀነስ ብልሹ አሰራርን እና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን የሚያስቀር ነው ተብሏል።



## የ54ቱ ማህበራት የስራ ሂደት ተገመገመ፡፡

በማህበር ተደራጅተው የጋራ መኖሪያ ቤት የሚገነቡ 54 ማህበራት ተወካዮች እና አማካሪዎች በተገኙበት ያሉበትን የስራ ሂደት የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ግምገማ ተደርጓል።



የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ክብርት ቅድስት ወ/ጊዮርጊስ መድረኩን ሲመሩ እንደተናገሩት ቢሮው በአሁኑ ወቅት ከአማራጭ የቤት ልማት አንዱ የሆነውን የማህበራት ቤት ግንባታ በልዩ ሁኔታ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እና ለግንባታው ተግዳሮት የሆኑትን ጉዳዮች ከባለ ድርሻ አካላት ጋር እየፈታ እየሄደ መሆኑን ገልጸዋል።

ሙሉ በሙሉ ወደ ግንባታው ለመግባት ማህበራቱም የሚጠበቅባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች በፍጥነት እንዲያጠናቅቁ አሳስበዋል።

ኢንጂነር መኮንን ሚጀና የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ በበኩላቸው ከመሰረተ ልማት ጋር ተያይዞ የተነሱ ችግሮች አብዛኛዎቹ የተፈቱና ቀሪዎቹ በመፈታት ሂደት ላይ ያሉ መሆኑን ተናግረዋል።

ስራውን ለማፋጠንም ከቢሮው በሁሉም ሳይቶች ላይ ክትትል የሚያደርጉ ባለሙያዎች መመደባቸውን ገልፀው ደረጃውን የጠበቀ ስራ ለመስራት ቅድመ ዝግጅቱ በጥሩ ሁኔታ ማለቅ አለበት ያሉ ሲሆን ስራ በፍጥነት ጀምሮ ለማጠናቀቅ ያግዛል ብለዋል።

በውይይቱም የተገኙት የማህበራቱ ተወካዮች የተለያዩ ጥያቄዎችንና ሃሳቦችን ያነሱ ሲሆን በስራ ኃላፊዎቹ ምላሽና ማብራሪያም አግኝተዋል።



## የመንግስት ቤቶችን መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማደራጀት ስራው ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

## ለቤቶቹም የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የመስጠት ስራም በፍጥነት ሊጠናቀቅ እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡

የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የመንግስት ቤቶችን መረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማደራጀትና ወደመረጃ ቋት የማስገባት፣ የመንግስት ቤቶችን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የመስጠት እና የአከራይ ተከራይ ውል ምዝገባ ስራ አፈጻጸምን በተመለከተ ከክፍለ ከተሞች የቤቶች ጽ/ቤት ኃላፊዎችና አስተባባሪዎች ጋር ውይይት አካሂዷል፡፡



ውይይቱን ያስጀመሩት የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ወ/ሮ ቅድስት ወ/ጊዮርጊስ ከቢሮው የ2017 በጀት ዓመት የትኩረት መስኮች አንዱ ቴክኖሎጂን ማዘመንና ስራዎችን በቴክኖሎጂ ተደራሽ ማድረግ መሆኑን ገልጸው የቤቶችን መረጃ በቴክኖሎጂ የማደራጀትና ወደ መረጃ ቋት የማስገባት ስራው በፍጥነት መጠናቀቅ እንደሚገባው አመልክተዋል፡፡

የአከራይ ተከራይ ውል ምዝገባ ሙሉ በሙሉ ባለመጠናቀቁና አዳዲስ ውል ምዝገባዎች መረጃ እየተለዩና እየተደራጁ ባለመሆኑ ስራዎችን በተቋሙ የመረጃ ቋት ላይ ለመጫን ክፍተት እየፈጠረ መሆኑን የገለጹት ኃላፊዋ ስራዎች በዝርዝር እየተለዩ መረጃዎች መደራጀት እንዳለባቸው አመልክተዋል፡፡

የመንግስት ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስራ አለመጠናቀቁ ቤቶችን በህገወጥ መልኩ ወደግለሰቦች እንዲዞሩ በር እየከፈተ እንደሚገኝም ኃላፊዋ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ከ150, 016 በላይ የመንግስት መኖርያና የንግድ ቤቶች መረጃ በለማው ቴክኖሎጂ ወደመረጃ ቋት ማስገባት እንደተቻለ ከነዚህ ውስጥ 93,350 የሚሆኑ ቤቶች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንደተሰራላቸው ለውይይቱ የቀረበው የበጀት ዓመቱ የ6 ወር ሪፖርት ያመላክታል፡፡



እስከአሁን ባለው ጊዜ ከ495,745 በላይ ቤቶችን የአከራይ ተከራይ ውል ምዝገባ መከናወኑን ሪፖርት ያሳያል፡፡

የቴክኖሎጂ ስራውን በቶሎ መጨረስ፣ ካርታ ያልተሰራላቸው ቤቶችን ካርታ የማዘጋጀት እንዲሁም የቤቶችን መረጃ የማደራጀትና ወደመረጃ ቋት የማስገባት ስራን በፍጥነት ማጠናቀቅ እንደሚገባም የቢሮው የአስተዳደር ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙሉነህ ፈይሳ አሳስበዋል፡፡

በመረጃዎች ምዝገባ ሂደት በልማት ምክንያት እየፈረሱ ያሉ ቤቶችን መረጃ በማቀናነስ መረጃዎችን ወቅታዊ ማድረግ እንዲሁም በፍርድ ቤት በክርክር ላይ ያሉ ፋይሎች በቶሎ እንዲቋጩና መረጃዎች እንዲደራጁ ማድረግ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም አቶ ሙሉነህ አሳስበዋል፡፡

ክፍለ ከተሞች ስራዎችን በፍጥነት ለማጠናቀቅ በቅንጅት መስራት አለባቸው ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው ስራዎችን የጨረሱ ክፍለ ከተሞች ሌሎችን ማገዝ እንደሚጠበቅባቸው ጨምረው አሳስበዋል፡፡

በዚህ ስራ ውስጥ የቢሮው የስራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ሊያደርጉ እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡



## የመንግስት እና የግል አጋርነት (PPP) ፕሮጀክት ትግበራ የ2017 በጀት አመት የ6 ወር አፈፃፀም ተገመገመ::

የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ፣ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን እና የመንግስት እና ግል አጋርነት ፅ/ቤት የስራ ኃላፊዎች የመንግስት እና የግል አጋርነት (PPP)



ፕሮጀክት ትግበራ የ2017 በጀት አመት የ6 ወር አፈፃፀም ገምግመዋል።

የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ ክብርት ቅድስት ወ/ጊዮርጊስ በግምገማው ወቅት እንዳሉት አፈፃፀሙ በየጊዜው እድገት የሚታይበት ነው ያሉ ሲሆን የጋራ መኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎችን የቤት ባለቤት ለማድረግ ከነበረው አካሄድ በላይ በመፍጠን 7/24 መስራት እንደሚገባ ገልፀዋል።
አቶ ሽመልስ ታምራት የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር በግምገማው ወቅት እንደተናገሩት ኮርፖሬሽኑ ሙሉ ሰአቱን በ70/30 ስራ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ በመሆኑ በየጊዜው ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል ብሏል።

ወደ ስራ ከገቡ አልሚዎች ጋር ቦርድ በማቋቋም እና በየጊዜው የአፈፃፀም ሪፖርት በመገምገም ፣ የመስክ ጉብኝት በማድረግ እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮችም ከስር ከስር በመፍታት ቀጣይ አቅጣጫዎች እየተሰጡ እየሄዱ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ አክለው ገልፀዋል።
ኢ/ር አስማማው ፈጠነ የምእራብ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምክትል ስራ አስኪያጅ ወደ ግንባታ የገቡ አልሚዎች ያሉበት የአፈፃፀም ደረጃ ፣ እየተሰሩ ያሉ እና ከእቅድ የዘገዩ ስራዎችን እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮችን በዝርዝር አቅርበው ውይይት ተደርጎበታል ።

## በአዲስ አበባ ቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የምዕራብ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ሕንፃ ግንባታ ተጠናቅቆ ለአገልግሎት ክፍት ሆኗል::

ቢሮው እና ኮርፖሬሽኑ እያካሄዱ ያሉትን አጠቃላይ ተቋሚዊ ለውጥ ( reform ) አንዱ ማሳያ ነው ተብሏል።
ክብርት ቅድስት ወ/ጊዮርጊስ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ በምርቃቱ ወቅት ተገኝተው እንደተናገሩት ፦
በምእራብ ቅ/ፅ/ቤት የተካሄደው ምቹ የስራ ከባቢን መፍጠር እና አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል ቢሮው እና ኮርፖሬሽኑ እያካሄዱ ላሉት አጠቃላይ ተቋሚዊ ለውጥ (reform) አንዱ ማሳያ ነው ብለዋል።



ከነበረው በላይ በመስራት ከተማ አስተዳደሩ እና ህዝባችን የጣለብንን ቤት ገንብቶ የማስተላለፍ አደራ ለማሳካት ከምንግዜውም በላይ ዝግጁ መሆናችንን ያሳያል ብለዋል ቢሮ ኃላፊዋ።





በቅርንጫፍ መስሪያ ቤቱ ደረጃውን የሚመጥን ምቹ የማገልገያ እና የመገልገያ በታ ተፈጥሯል ፤ ከብልሽት ነፃ የሆነ ፣ የተቀላጠፈ እና ከእጅ ንክኪ የፀዳ አገልግሎት ለመስጠት ያግዛል ያሉት ደግሞ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ ታምራት ናቸው።

## ወደ ጋራ መኖሪያ ቤት እየገቡ የሚገኙ የልማት ተነሺዎችን ነባሩ ነዋሪ በአግባቡ ተቀብሎ ማኖር አካባቢውን ማልማት እና በጋራ ማደግ ይገባል።
## አቶ ሙሉነህ ፈይሳ
## የቤቶች ልማት እና አስ/ቢሮ ም/ቢ/ኃላፊ

የቤቶች ልማት እና አስተዳዳር ቢሮ እና የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን ከጋራ መኖሪያ ቤት ማህበራት ተወካዮች ጋር ውይይት አካሂደዋል።

አቶ ሙሉነህ ፈይሳ ውይይቱን በንግግር ሲከፍቱ እንዳሉት በለውጥ ውስጥ ለምትገኘው ከተማችን እየተሰራ ላለው ልማት ቢሮው እና ኮርፖሬሽኑ በርካታ ቤቶችን በጥራት እና በፍጥነት በመገንባት ለልማት ተነሺው ማስተላለፋቸውን ጠቁመው ወደ ጋራ መኖሪያ ቤት እየገቡ የሚገኙ የልማት ተነሺዎችን ነባሩ ነዋሪ በአግባቡ ተቀብሎ ማኖር አካባቢውን ማልማት እና በጋራ ማደግ ይገባል ብለዋል።

ኃላፊው አክለውም በመቀራረብ ፤ ነዋሪውን በማሳተፍ ፤ ነዋሪው ሲገባና ሲወጣ ዋስትናውን መጠበቅ እና አካባቢውን ንፁህ አረንጓዴ እና ውብ ማድረግ ይገባልም ብለዋል።



ቤታችሁንም አካባቢያችሁንም እያፀዳችሁ ለኑሮ ምቹ በማድረግ ማህበራቶች ነዋሪዎችን አስተባብራችሁ ተግባብታችሁ እንድትኖሩ አደራ ያሉት ደግሞ ኢ/ር መኮንን ምጀና የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ም/ቢሮ ኃላፊ ናቸው ።



ኢ/ር ቶማስ ደበሌ የቤቶች ልማት ኮርፖሬሽን የቤት ማስተላለፍ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር በበኩላቸው

የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎች ዛሬን በመተባበር ፤ አብሮ በመኖር ፣ በመደጋገፍ እና በመተሳሰብ ፤ ነገን እየሰራችሁ በጋራ በመለወጥ መሻገር ያስፈልጋል ብለዋል።
የማህበራት ተወካዮች በበኩላቸው ለነዋሪው ሞቅ ያለ አቀባበል በማድረግ በደስታ እየተቀበሉ መሆኑን እና አብረው ለመኖርም ዝግጁ መሆናቸውንም ገልፀዋል።





ለውይይቱ መነሻ ሰነድ ያቀረቡት አቶ አብዲሳ አራርሶ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ፅ/ቤት ኃላፊ ናቸው።

## በቢሮው የተካሄደው ሪፎርም ያመጣው ውጤታማነት ተገመገመ።

ግምገማውን የተካሄደው በፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ የሪፎርም ጥናት ቡድን ሲሆን አላማውም ለሪፎርም ስራው ገፊ የነበሩ ምክንያቶች መቀረፋቸውን፤ ሪፎርሙ ምን ጉድለት እና ጥንካሬ ነበረው እና አላማውን አሳክቷል ወይ የሚለውን ታሳቢ ያደረገ ነበር።
በግምገማው ወቅት ክብርት ቅድስት ወልደጊዮርጊስ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ እንደተናገሩት ተቋሙ ባካሄደው ሪፎርሙ በዋናነት ስራዎችን በቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ማድረጉ ለሪፎርሙ እንደ አንድ ገፊ ምክንያት የነበረውን ሌብነት እና ብልሹ አሰራር ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር እየቀረፈ የመጣ መሆኑን ገልፀዋል።



በተለይም በሪፎርሙ የአከራይ ተከራይ ስራን በተሳካ ሁኔታ ማካሄዱ እና የኮሊደር ልማት ተነሺዎችን ምትክ ቤት እጣ አወጣጥ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ማድረግ በመቻሉ የሚነሱ ቅሬታዎች መቀነሳቸው የሪፎርሙ ውጤት ማሳያ ናቸው ብለዋል።
ከሪፎርሙ ወዲህ የተቋሙ የመፈፀም አቅም ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻለ መምጣቱን እና ቢሮው ከክፍለ ከተማ እስከ ወረዳ በመናበብ እየሰራ መሆኑን ደግሞ አቶ ሙሉነህ ፈይሳ የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ም/ቢሮ ኃላፊ አሳውቀዋል።
ተቋማዊ ማሻሻያ የተደረገበትን ምክንያት እና የመጣውን ለውጥ አቶ አብዲሳ አራርሶ የቢሮው ፅ/ቤት ኃላፊ ለገምጋሚ ቡድኑ በዝርዝር አቅርበዋል።
ከፐብሊክ ሰርቪስ እና ሰው ሀብት ቢሮ የመጣው ገምጋሚ ቡድን አባላትም በቢሮው የተሻለ አፈፃፀም መኖሩን በተለይም ምቹ የስራ ቦታ መፈጠሩን እንዲሁም ስራዎች በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ መደረጉን እና ሌሎች በርካታ ለውጦች መመልከታቸውን ገልፀዋል።

## የመንግስት ፣ የጋራ እና የግል መኖሪያ እንዲሁም ንግድ ቤቶችን መረጃ ወደ ከተማ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ሲስተም (UHDMS) በማስገባት አገልግሎቶች በቴክናሎጂ ተደግፈው እንዲሰጡ በአስራ አንዱም ክፍለከተሞች ክትትል እና ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል።

የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ በአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች የሚያደርገው ክትትል እና ድጋፍ የከተማ ቤቶች መረጃ ሲስተም አገልግሎት ማስጀመር፤የመንግስት ቤቶች ካርታ እንዲሰራ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ፤ የመደበኛ ቤት ከራይ ውል ምዝገባ እና እድሳት ስራዎች የተመለከተ ነው።

ዓላማውም ከተማ አስተዳደሩ የሚያስተዳድራቸው የመንግስት ቤቶች ፤የጋራ መኖሪያ እና ንግድ ቤቶች እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ የግል መኖሪያ ቤቶች መረጃ ወደ ከተማ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ሲስተም (UHDMS) በማስገባት አገልግሎቶች በቴክናሎጂ ተደግፈው እንዲሰጡ ለማድረግ ነው ተብሏል።



የቤት መረጃ ሙሉ በሙሉ በዘመናዊው ሲስተም ሲሆን የተዝረከረኩ እና ብልሹ አሰራር የተጋለጡ አሰራሮችን የሚያስቀር እንዲሁም የቤት መረጃን ለተፈለገው አላማ ለመጠቀም የማያመች በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ነው ተብሏል።

ስራውን በተገቢው መንገድ በመምራት ክፍለ ከተሞቹ ወደ ተግባር እንዲገቡ ለማስቻል ቢሮው ከፍተኛ አመራሮችን እና ዳይሬክተሮችን በአራት ቡድን አዋቅሮ በማሰማራት እስከ ጥር 30/2017 ድረስ ክትትል እና ድጋፍ እንዲያደርጉ እና አስራ አንዱም ክፍለከተሞች ሙሉ በሙሉ ወደ ተግባር እንዲገቡ እየተሰራ ይገኛል ።

## ቢሮው በቤት ልማት ስትራቴጂና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ዙርያ በማእከል ለሚገኙ ዳይሬክተሮች እና ለክፍለ ከተሞች የቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊዎች ስልጠና ሰጥቷል።

የመኖርያ ቤት ችግር በዘላቂነት ለመፍታትም በመንግስት
9O5A2790.JPG
አስተባባሪነት የሚካሄደው የቤት ልማት ስትራጂዎች በተጨማሪ ቢሮው ሌሎች ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ እየተገበረ እንደሚገኝ የገለጹት የቤት ጥናትና ስትራቴጂ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ኤርሚያስ ውበት በግል ባለሀብትና በመንግስት አጋርነት፣ የመኖርያ ቤት ሽርክና በማቅረብ፣ በመኖርያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር፣ በሪል ስቴትና በግል ቤት አልሚዎች ቤቶች ማቅረብ የስትራቴጂው አካል መሆናቸውን ገልጸዋል።

ለስትራቴጂው ስኬታማነት ፈጻሚዎችና ባለድርሻ አካላት በስትራቴጂው ምንነት፣ አስፈላጊነትና የአፈጻጸም አቅጣጫዎች ላይ እውቀቱና የጋራ መረዳት ሊኖራቸው እንደሚገባ ተናግረው የተዘጋጀው ስልጠና ዓላማም ሰልጣኞች በስትራቴጂው የጋራ ግንዛቤ እንዲይዙና በቀጣይ ውጤታማ ስራ ለመስራት የሚያስችል አቅም ለመፍጠር መሆኑን ገልጸዋል።



ስልጠናውን የሰጡት የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር አማካሪ አቶ በየነ መሰለ የቤቶች ልማት ስትራቴጂና ፖሊሲ

ዋና ዓላማ ነዋሪዎች በተመጣጣኝ ዋጋ አቅምን ያገናዘበ መሰረተ ልማቶች የተሟሉለት ተደራሽ ቤት የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

የቤት ልማት ትግበራን ታሪካዊ ዳራ የዳሰሱት አሰልጣኙ በቤት ልማት ስትራቴጂው የተከናወኑ ተግባራትን፣የተገኙ ውጤቶችንና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን አብራርተዋል፡፡

እየተተገበሩ ያሉና ሊተገበሩ የታሰቡና የቤት ልማት አማራጮችንም አመላክተዋል፡፡

የቤት ፋይናንስ አቅርቦት እጥረት፣ ለቤት ግንባታ የሚውል የመሬት ዝግጅትና አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን፣ የግንባታ ግብዓቶች እጥረትና የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ አቅም አናሳ መሆን፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦ ችግር መኖር፣ በየጊዜው እየጨመረ የመጣው የከተማ ነዋሪዎች ቁጥር ለቤት ልማት ስተራቴጂው ስኬታማነት አሉታዊ ተጽዕኖ እንደፈጠሩ በስልጠናው ተብራርቷል፡፡

በቀጣይ የቤት ልማት ፖሊሲውና ስትራቴጂው በቂ የቤት ግንባታ መሬት ማቅረብ፣ አማራጭና ተደራሽ የቤት ፋይናንስ ስርዓትን መዘርጋት፣ የግል ዘርፉን ተሳትፎ በማሳደግና የኪራይ ቤት አቅርቦት አማራጮችን እንዲሰፋ በማድረግ ተደራሽነቱን ለማስፋት ትኩረት ተሰቶት እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡



## ሙያና ሙያተኞች በስነምግባር ካልታነፁ የተቋም እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል ተባለ፡፡

ይህም የተገለፀዉ በአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ሰራተኞች የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት ባዘጋጀው ሙያዊ ስነ ምግባር ግንባታ ላይ በተሰጠ ስልጠና ላይ ነው፡፡
ስልጠናውንም በንግግር የከፈቱት የቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ የፅ/ቤት ኃላፊ አቶ አብዲሳ አራርሶ ሲሆኑ ስልጠናው ሙያና ሙያተኞች በስነ ምግባር ካልተመሩ እና ካልታነፁ የተቋማት እድገት አሉታዊ ዉጤት ሊይዝ ይችላል ብለዋል ፡፡




በተናጠል ሁሉም የራሱ ሙያዊ ስነ ምግባር ሲኖረዉ እንደ ተቋም የጋራ የሆነዉን የስራ ስነ ምግባር ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል ብለዋል፡፡
የውይይቱን መነሻ ሰነድ ያቀረቡት የቢሮው የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ፈይሳ ረጋሳ ሲሆኑ የሰነ ምግባር ፅንሰ ሀሳብ ፤ ሙያና ሙያተኛ መረዳት እንዲሁም የሙያ ስነምግባር አስፈለጊነት የሚሉ ርእሶችን ዳሰዋል ፡፡




ስነምግባር በተቋማት ሰላምን ከማሰፈን ፤ እኩልነት ለማረጋገጥ ፤ አካታች ስርዓት እንዲኖር እንዲሁም የጋራ እድገትን ለማምጣት ከፍተኛ ሚና እንዳለውም ተናግረዋል፡፡
በቀጣይም ሠራተኞች በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ በተቋሙ እንደ ችግር የሚነሱ የሰዓት አለማክበር ፤ የታማኝነት ችግር እንዲሁም ጥሩ ያልሆነ የስራ ስነ ምግባርን በመፍታት የመስሪያ ቤቱን እሴት በማክበር ፤ ኃላፊነት የሚሸከም እና የማህበረሰቡን ጥቅም የሚያስቀድም የተሟላ ስብዕናን የተላበሰ አመራርና ሰራተኛ መፍጠር ይገባል ሲሉ ገልፀዋል ዳይሬክተሩ ፡፡

## ቢሮው በቋሚነት ለሚደግፋቸው ቤተሰቦች የገና እና የጥምቀት በአልን ምክንያት በማድረግ የቁስና የገንዘብ ድጋፍ አደረገ።

የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ አመራሮችና ሰራተኞች የተዘጋጀውን ስጦታ በቢሮው እናት አምባሳደሮቹ አስተባባሪነት በመኖሪያ ቤታቸው በመገኘት ስጦታውን አበርክቷል ።

ቤተሰቦቹ በቋሚነት እየተደረገላቸው ባለው ድጋፍና አሁን በተሰጣቸው ስጦታ ምስጋናቸውን አቅርበዋል። ቢሮው በቋሚነት ሶስት ቤተሰቦች እና 4 ህፃናትን መደገፉ ይታወቃል።





ዜና ቤቶች ቅጽ 1 ቁጥር 3 የታህሳስ እና ጥር ተ!!!

## የአዲስ አበባ ቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ ማህበራዊ ድረገጾች

https://linktr.ee/aahdab